.

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም.

## *የሰማዩም የምድርም ግማሽ ባለቤቶች ሴቶች ናቸው!!*

የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም.(ማርች 8 ቀን) አለም አቀፍ የሴቶች ቀን በመላው አለም ለሴቶች መብት መከበር በሚታገሉ የተለያዩ በርካታ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ድርጅቶች አማካኝነት ባለፉት ጊዜያት የተሰሩና በእቅድ ተይዘው ነገር ግን ያልተሰሩ ዘገባዎችን ያዘለ፡ በትግሉ የተሰዉትን የሚዘክር ወደፊትም መተግበር የሚገቡትን አስመልክቶ የተለያዩ መግለጫዎችን ይፋ በማድረግ በተለየና በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ ይውላል። ሴቶች ነክ የሆኑ ከሰላማዊ ሰልፍ አንስቶ ትያቲሮችን፡ ፊልሞችን፤ የቅስቀሳ መጣጥፎችን የመሰሉ ዝግጅቶችን ባካተተ ፕሮግራም የታጀበ ብቻ ሳይሆን ለሕብረተሰቡና በሥልጣን ላይ ለሚገኙ ኃላፊዎች እንዲሟሉ የሚፈለጉ ጥያቄዎችን በማቅረብም የሚጠናቀቅ ነው።

የዘንድሮው ዝግጅትና አከባበር ልዩ የሚያደርገው ይህ ቀን በአለም አቀፍ ደረጃ መከበር ከጀመረ 100 ኛ አመቱን በማስቆጠሩና በአካባቢው ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ደረጃ የአለምን ሕዝብ ባስደነቀ መልኩ ሴቶች በስፋት የተሳተፉበት በሰሜኑ አፍሪካ የለውጥ ሕዝባዊ አመፅ በዚሁ አመት ተጀምሮ በቱኒዚያና በግብፅ የአምባገነን ሥርአት ቁንጮዎችን በማስወገድ ለዘላቂ ለውጥ መገኘትም በከፍተኛ ደረጃ ትግላቸውን እየቀጠሉ ባሉበት፡ በሊቢያም ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ድልን ለመቀዳጀት በትንቅንቅ በሚገኙበት ወቅት ለመከበር በመቻሉ ጭምርም ነው። በተለይም ከተለያዩ የአለም አካባቢ ተወካዮች የሚሳተፉበት በሼኑንዙላ ለጋራ መተባበር፡ ተመክሮን ለመለዋወጥ፡ ስለ ሴቶች የፖለቲካ፤ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ ለመወያየት፡ የጋራ ዕቅድን ለመትለም፡ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ እንዲጠናከር የጋራ ውሳኔ የሚወስኑበት ስብሰባ መደረጉ ለበአሉ ድምቀት የራሱን አስተዋፅዖ አበርክቷል።

ይህ በሰሜን አፍሪካ የተጀመረው ሕዝባዊ የአመፅ እንቅስቃሴ ከአካባቢው አልፎ በአፍሪካ ቀንድ ጎረቤት የመንና ባህሬይ ጭምር በርካታ ሴቶች ተካፋይ እየሆኑ ያሉበት፡ የመብት መከበር ትግል መካሄድም ለሴቶች ትግል የራሱን አሻራ የሚያሳርፍና ለሌላውም በተመሳሳይ ሁኔታ ለሚገኙ ሕዝቦች ተመክሮ የሚገኝበት በመሆኑ ለቀኑ መከበር የበለጠ ድምቀት እያስገኘለት ይገኛል።

አለም አቀፍ የሴቶች ቀን ታሪኩ ለማህበራዊና ለፖለቲካ ፍትህ መገኘት የተደረገ የፖለቲካ ታሪክ ነበርና አሁንም ነውና ይህ ለሴቶች ትግል መለያና የማንነታቸው መግለጫ የሆነውን ቀን ለዴሞክራሲ፡ ለሰብአዊ መብትና ለሕብረተሰባቸው አጠቃላይ እድገት የቆሙ ሰላም ወዳድ ኃይሎች በሙሉ የበአላቸው ተካፋይ በመሆን የትግል አንድነታቸውን የሚገልፁበት ቀን ነው።

የኢትዮጵያ ሴቶችም እንደ ጾታ አምሳያቸው ሁሉ ይህን የነሱን ቀን በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ሀገር አመቺ ሆኖ ባገኙት ሁኔታ ለማክበር በዝግጅት ላይ ናቸው። የኢትዮጵያ ሴቶች ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ለመገንባት በተደረገው የ3000 አመት የታሪክ ሂደት ከወንድሞቻቸው ያላነሰ አኩሪ ገድል የፈፀሙና ከፍተኛ መስዋዕትነትም የከፈሉ ለመሆናቸው በታሪክና በተኪዎቻቸው ሕሊና ውስጥ የተቀመጠ ነው። በቅርቡ በተከበረው

115 ኛው የአድዋ ድል ቀን መታሰቢያ ስማቸውና ገድላቸው እየተነሳ ሲዘከሩ የነበሩት ሴቶች ጀግኖቻችን ለዚህ ጉልህ ምስክር ነው። ይህ ሆኖ ሳለ የመብት መከበርን በተመለከተ በሴትነታቸው እየደረሰባቸው ያሉት የተለያዩ በደሎችን በማስወገድ ለእድገታቸው መሰረት የሚሆን የነፃነት አየር ለመተንፈስ ገና አልታደሉም። የፆታ እኩልነታቸው አልተረጋገጠላቸውም።

የሩቁን ለጊዜው በታሪክነቱ እናቆየውና የቅርቡን የባላባታዊ አገዛዙንና ሥርአቱን ለማስወገድ በተደረገው ሕዝባዊ አብዮት ውስጥ አኩሪ ታሪክ ቢያስመዘግቡም የሕዝቡን ድል በመንጠቅ ከሥልጣን የተቆናጠጠው የደርግ አገዛዝ አምባገነናዊ ሥርአቱን በማስፈን፤ የነበረውን ጭቆና ከማጠናከሩ ባሻገር እንደ ወንድሞቻቸው ሁሉ ሴቶችንም ለአሰቃቂና አሳዛኝ ጭፍጨፋ ዳርጓቸዋል። ይህ አረመናዊ አገዛዝ እንዲወድቅ ለ17 አመታት ያለመታከት አሁንም ለትግሉ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ቢያበረክቱም እሱን የተካው የወያኔ አገዛዝ በበኩሉ ከደርግ በባሰ ሁኔታ ዘረኛና አድሃሪ ሥርአት ገንብቶ፣ ዜጎችንም በክልል አጥሮ ቀድሞውኑ ይደርስባቸው የነበረውን በደል በባሰ መልኩ ቀጣይ እንዲሆን እያደረገ ይገኛል። የሴቶችን እኩልነት በተግባር የሚያረጋግጥ አንቀፅ በሕገ አገዛዜ አስፍሬያለሁ እያለ ነጋ ጠባ ቢለፍፍምና ቢመፃደቅም ለሴቶች የእኩልነት መብት ተቆርቋሪ ነኝ እያለ የባዕዳንን ጆሮ ሳይቀር ቢያደናቁርም በአገዛዙ በኩል ለሴቶች የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ ሴቶች በሁሉም መልክ ያላቸው ተሳትፎ ከወንዱ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ወደኋላ የቀረ መሆኑ፣ ዛሬ ብዙሃን ሴቶች ከየመድረኩ ተገለውና ተጨቁነው መገኘት፣ የሴቶች እኩልነት በጥቂት ሴቶች በመለስ ዜናዊ ፍቃድ በሚኒስትርነትና በዳይሬክተርነት መሾም የሚገለፅ ባለመሆኑና ፆታቸውን ተንተርሶ በገጠርም በከተማም ኗሪ በሆኑ ሴቶች የሚደርሰው በደል መባባሱ የሚያረጋግጠው አንድ ሀቅ ቢኖር ይህንኑ ነው።

ባለፈው አረመኔውን የደርግ አገዛዝ ከሕዝብ ጫንቃ ለማውረድ በተደረገው መራራና እልህ አስጨራሽ ትግል በብዛት ተሳትፏቸው አኩሪ ታሪክ ያስመዘገቡ እናቶቻችን፣ እህቶቻችን፣ የትዳር ጓደኞቻችን፣ ወጣት ሴቶቻችን የትግል ፍሬያቸውን ለማየት አልታደሉም። በትግሉ ወቅት የከፈሉት መስዋዕትነት ያነሰ ይመስል በመለስ አገዛዝ ምክንያት ስቃያቸው የበለጠ እየተባባሰ፣ በተለያየ አንፃር እየተበደሉ፣ እየተጠቁ በውድ ሀገራቸው በሁለተኛ ደረጃ ዜግነት ተፈርጀው የሚገኙ ናቸው። በባህልም፣ በማህበራዊ ኑሮ፣ በፖለቲካው፣ በኤኮኖሚው ባጭሩ በሥርአቱ ውስጥ ከወንዱ በበለጠ ተበዳይ የሆኑት ሴቶች ናቸው። አሁንም ጎጂ ባሕሎች በሕግ የመጠየቃቸው ሁኔታ በባህል ማክበር ምክንያት እየተሳበበ ሕጋዊ እርምጃ አይወሰድም። ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ወጣት ልጃገረዶችን መጥለፍና አስገድዶ መድፈር ዛሬም ያለ ነው።

ማህበራዊ ቀውሶች መፍትሄ ባላገኙበትና ይበልጡኑም እየተባባሱ በሚሄዱበት እንደ ኢትዮጵያ በመሳሰሉ ሕብረተሰብ ውስጥ የዚህ ገፈት ቀማሽና የቀውሱ ሰለባ የሚሆኑት የሕብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶችና እንዲሁም ሕፃናት ናቸው። በመሆኑም በጣም አስከፊና ትውልድ መታሪ በሆነው የኤድስ ቀሳፊ በሽታ ከተለከፉት ዜጎቻችን መሃል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። ከዚህ አይነት አሳዛኝና አሰቃቂ የኑሮ ሁኔታ መፍትሄ ባለማግኘታቸውና ያልፍልኝ ይሆናል በሚል ቀቢሰ ተስፋ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ለገና ወጣት ሴቶች በተለያዩ የአረብ ሀገሮች ጉልበታቸው እየተበዘበዘ፣ ሰብዕናቸው እየተዋረደ፣ ክብረ ሕሊናቸውን እያሰቀቁ ብቻ ሳይሆን ዘረኝነት በሚያጠቃቸው አሰሪዎቻቸውና ቀጣሪዎቻቸው በግዴታ የወሲብ ተግባር እየተፈፀመባቸው የሚኖሩ እንዳሉና የድረሱልን መልዕክትም እያስተላለፉ ይገኛሉ። ለዚህም ተጠያቂው ሌላ ሳይሆን የመለስ አገዛዝ መሆኑ ግልፅ ነው።

ምንም እንኳ የሴቶች ቁጥር ከወንዱ የሚበዛ ቢሆንም የትምህርት እድል ለማግኘት የሚችሉት ሴቶች ቁጥር በጣም ትንሽ ነው። በተለያዩ እስር ቤቶችና ማጎሪያዎች የሚገኙ ሴቶች፣ ደብዛቸው የጠፋ፣ በግዳጅ የተደፈሩ፣ የተገደሉ ቁጥራቸው በርካታ ነው። በድህነት፣ በጤና አገልግሎት፣ በትምህርት እድል፣ በማህበራዊ ኑሮ፣ የወጣት ሴቶች መንገድ አዳሪነትና ለወሲብ ባርነት፣ በአደንዛዥ ዕፀዋት ሱስ መለከፍ፣ ለወንዶች ብዝበዛና ዋልጌነት መዳረግ፣ ለድብደባና ጨካኝ ቅጣት መጋለጥ፣ ቀኑን እየጠበቀ በሚመጣው ረሃብ ችግር በብዛት ሰለባ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። እነዚህን በመሳሰሉት የጭቆናና የበደል መስኮች ሴቶች እየደረሰባቸው ያለውን ጭንቀት፣ የመንፈስ መረበሽ፣ ለሚገነዘብ ሰብአዊነት ላልተለየው ማንኛውም ዜጋ ሁሉ በውነትም

**አስተዳድረዋለሁ ለሚል መንግሥት ቀርቶ ለራሱ ለሕብረተሰቡም ቢሆን የሚያሳፍር ሁኔታ ነው። ሊያስወግደውም የሚገባ ነው። ከማስወገድ በቀር ሌላ ምንም ምርጫም የለውም።**

**በመሆኑም የኢትዮጵያ ሴቶች ነፃነታቸውን ለመጎናፀፍና መብታቸውን ለማስከበር ወደፊት ገና በፅናት መታገል ዛሬም ግዴታን ጠያቂ ሆኖ ይገኛል። በኢትዮጵያ በአገዛዙና በወንዱ አማካኝነት በሴቶቻችን ላይ የሚደርስባቸው በደል፣ ጭቆና፣ መከራና ስቃይ ሥር የሰደደ በመሆኑ መፍትሄውም ጥገናዊ ለውጥ ሳይሆን በሕዝባዊ አመፅ በሚፀነስ መሰረታዊ ለውጥ የሚገኙ ለመሆኑ ግልፅ ነው። በዚህም ምክንያት አለም አቀፍ የሴቶች ቀን ለፆታ እኩልነት መስፈንና ለመብት መከበር የፀና ትግል እንዲደረግ የሚጋብዝ ቀን የሚሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በኢትዮጵያ ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ሁሉንም አይነት በደል በጥብቅ የሚቃወም በመሆኑ ለሕዝብ ቀናኢና ሀገር ወዳድ የሆኑ ሁሉ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች በሁሉም መስክ ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው እንደ ዜጋ መብታቸው ታውቆና ተከብሮ ለሀገራቸው እድገት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ የሚያስችላቸው የፖለቲካ ምህዳር ይፈጠር ዘንድ ትግላቸውን እንዲያጠናክሩ ጥሪውን ያቀርባል።**

**የሴቶች መብት በፀና ትግል ይረጋገጣል!!**
**ከሴቶች ትግል ጎን መሰለፍ ሀገር ወዳድነት ነው!!**

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM